# አልጋ ወራሽ ሀይለማሪያም ደሳለኝ
## ከአቶ መለስ የተረከቡት አደራ ምንድን ነው?

ከበላይ ገሠሠ
ሰሜን አሜሪካ

## ክፍል አንድ

በአቶ መለስ ዜናዊ የአስተዳደር ዘመን እያንዳንዳችን ቢያንስ አንድ ነገር እናስታውሳለን ብዬ እገምታለሁ። እንደኔ አመለካከት አቶ መለስ ዜናዊ ጫካ ከገቡበት ቀን ጀምሮ እስከ ህልፈተ ቀናቸው ድረስ የዓይን ብሌናቸው የሆነውን ስልጣን ከእጃቸው እንዳያመልጥና ክፍተት እንዳይፈጠር ለማድረግ ሳይተኙ ሌሊት ተቀን ዕረፍት አጥተው ይሰሩበት የነበረና ዛሬ ለአልጋ ወራሽ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ካወረሱዋቸው ፍልስፍናዎች፣ ፓሊሲዎችና ስትራተጂዎች ውስጥ የሚከተሉት 10 ነጥቦች በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው ብዬ አምናለሁ። እነሱም፦

1) ውሸት በማር ጠቅልሎ ማጉረስ። በሬ ወለደ ብሎ በአደባባይ የማሳመን ችሎታና ራሱ ገርፎ ራሱ የመጮኽ ልምድ
2) ስድብና ሽብር የአገዛዝ መርሃ ጥበብ (ፕሮፌሽናል ስራ) አድርጎ መከተል። የሌላውን ዜጋ የትግል ወኔ በማደድልና በማንቋሸሽ የራስህን ገናናነትና ታሪክ መገንባት፣ መሳደብና ማሸበር እንደ ትልቅ የአዋቂነትና የጀግነነት መለኪያ አደርጎ መቁጠር
3) የለያይተህና አናቁረህ ግዛ ኢንጂነሪንግ። እሾኽን በእሾኽ በማዋጋት ህዝቡ መብቱን የማስከበር ዓቅም ማዳከም (የብሄር ብሄረሰብ ጠበቃ መስሎ በመታየት አንዱ በሌላው ወንድሙ ላይ ጥላቻና ጥርጣሬ እንዲኖረው ማድረግ)
4) በፍርሃትና በሽብር አዋጅ ዜጎች የኢሕአዴግ ምርኮኛ በመሆን ባርነትን አሜን ብለው እንዲቀበሉ ማድረግ
5) በነቀዘ ኢኮኖሚ ህዝቡን የህልም እንጀራ ማብላት። ድህነትንና ኋላቀርነትን ለፓለቲካ መሳሪያነት በመጠቀም ህዝቡን በሆዱ እንዲቀጣ ማድረግ
6) ለጋ ትውልድ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አመለካከት ማደንዘዝና መሸበብ። ለመብቱ የሚታገል ዜጋ እንዳይበቅል በማድረግ አልፋ -ወ- ኦሜጋ የመቶ ዓመት ስልጣን ህልም እውን ለማድረግ በቀጣይነት ጥረት ማድረግ
7) የባዕድ መሳሪያነትና ሎሌነት (ጥገኝነት)። ስልጣን ከሀገርና ከህዝብ ሉዓላዊነት በላይ በማስቀደም የሀገር ሀብት፣ የህዝብዋ ክብርና ብሄራዊ ጥቅም ለባዕድ አሳልፎ መሸጥ
8) ምንቀኝነትና ቂም በቀል ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ በሽታ እንዲሆን ማድረግ። ጥላቻን በመቆስቆስ በህዝብ መካከል አለ መተማመንና ጥርጣሬ እንዲነግስ ማድረግ
9) የተኰላሸ ታሪክ፣ የተበረዘ ባህል፣ የተዳከመ ኢትዮጵያዊነትና የብሄራዊ እሴቶቻችን ፋብሪክ ቀስ በቀስ በማጥፋት በስታሊናዊ የግንጠላ ሪእዮት እንዲተካ ማድረግ
10) ለኤርትራ ነፃነት ከኤርትራዉያን በላይ ጥብቅና በመቆምና በትግራይ ህዝብ ደም በመነገድ ኢትዮጵያ በታሪክ እንድትቀጣ በማድረግ ወደብ አልባ የሆነች ሽባ ሀገር ማውረስ የመመሳሰሉ ናቸው።

በነዚህ 10 ነጥቦች ዙሪያ በሀገርና በወገን ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች፣ ክሕደቶች፣ ማጭበርበርና አፈናዎች ብዙ ቢሆንም በዚህ አጭር ፅሑፍ ሁሉንም ዘርዝሮ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማቅረብ ለቀባሪ ማርዳት ስለሚሆንብኝ ሌላውን ለታሪክ ፀሐፊዎች ትቼ ለዛሬ ያልኩዋቸው ብቻ ጥቂት ልበል። ምናልባት በጠቀስኩዋቸው 10 ነጥቦች ላይ ለመጨመር፣ አስተያየት ለመስጠትም ሆነ ለመቃወም የምትፈልጉ ወገኖች ካላችሁ በማንኛውም ነፃ መድረክ መፃፍ ወይም መከራከር እንደሚቻል በዚሁ አጋጣሚ ልገልፅላችሁ እወዳለሁ። በተረፈ አልጋ ወራሽ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ከአቶ መለስ የተረከቡት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ከመመለሴ በፊት እስቲ ከህዝብ አባባሎች ውስጥ አንድ ሁለት ጠቅሼ ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ልመለስ።

በአንድ ወቅት አንዲት ሴት አልቃሽ ብዙ ህዝብና ወላጅ ዘመድ በተሰበበት በአንድ ታዋቂ ባለባት የቀብር ስነ ስርዓት ተገኝታ **"እዩት ይቺን ዓለም እኛን ስታታልል-የሞተ ሰው የነበረ አይመስልም! ያለው ደግሞ የሚሞት አይመስለውም"** በማለት ሃዘንዋን በሰው ልጅ ከንቱነት ገለፀች ይባላል። አምባ ገነኖች ሞት በአጠገባቸው የማታልፍ እየመሰላቸው ዘላለም የሚኖሩ ምድራዊያን መላእክት አድርገው በመቁጠር የህዝብ አፍ ዘግተው ገደብ የለሽ የገነቡት ስልጣን እንደ ባቢሎን ግንብ በአንድ ጀምበር ሲፈራርስ ማየቱ ምንኛ ያስገርማል። ነገር ግን ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነውና የሚያስገርመው ስለላለፉት መሪዎችና አምባ ገነኖች አይደለም። ሞት'ማ የማይቀር የሁላችን ዕዳ ነው። ነገር ግን ማዘን ያለብን ካለፈው ሳይማሩ ዛሬም አቶ መለስ ዜናዊ የሰጡን ባርነት ወራሾች ነን እያሉ በመናገር የገዛ ስብእናቸውንና ህሊናቸውን ሸጠው በቁሙማቸው ስለተቀበሩ መሪዎች ነው። እነዚህ መሪዎች እነ ማን ናቸው? ትሉ ይሆናል። መልሱ ቀላል ነው። ለዚሁ ገላጭ የሆነውን አንድ ወጣት የነገረኝን አስቅኝ ገጠመኝ በድጋሚ ልጥቀስላችሁና ወደ ቀጣዩ ልለፍ።

አቶ መለስ ዜናዊ በስልጣን በነበሩበት ዘመን ከኢትዮጵያ ዲቪ ሎተሪ ደርሶት ወደ ሰሜን አሜሪካ የመጣ አንድ ወጣት ኢትዮጵያዊ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በሕብረተ ሰቡ ዘንድ በየጎዳናው ሲነገር የሰማውን የህዝብ አባባል ብሎ ያወጋኝን አጭር አስቂኝ ገጠመኝ እኖሆ እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል። እሱም እንዲህ ይላል። “ፀረ ሙስና ኮሚሽን እንደ ተቋቋመ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ያላቸውን ሀብት እንዲያስመዘግቡ ባወጣው መመሪያና ዕቅድ መሰረት ምዝገባውን ከላይ በከፍተኛ ባለስልጣኖች ለመጀመር ወደ ዋናው ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ይሄዳል። እዚያው እንደ ደረሰም አቶ መለስ ዜናዊን በቢሮዋቸው አግኝቶ ያላቸውን ንብረት በዝርዝር እንዲያስመዘግቡ ይጠይቃቸዋል። አቶ መለስም በተለመደው አንደበታቸው ባልተጠበቀና በሚያስገርም መልኩ እንዲህ በማለት ተናገሩ። “እኔ በባንክ ያስቀመጥኩት ጥሬ ገንዘብ የለኝም። አሁን እጄ ላይ ያሉኝ ንብረቶች የሚከተሉት ናቸው

- ትልቁ የማይንቀሳቀስ ንብረቴ ፕረዚዳንት ግርማ ወለየስ ናቸው
- ተንቀሳቃሽ ንብረቴ አባ ዱላ፣ አባይ ወሉና በረከት ስምዖን ናቸው
- ያለኝ የመሬት ሀብት ደግሞ አንቀፅ 39 ነው
- ሌላው ንብረቴ ከስታሊን የወረስኩት መፅሐፈ ስርየት ነው።
  መፅሐፉም “ፍካረ መለስ” ተብሎ የዚሁ ትውልድ መማሪያ እንዲሆን ለሁሉም ትእዛዙ ተላልፏል
  በማለት ቁርጥ ያለ የማያሻማ መልስ ሰጡ” ሲል ሳቅና ቁጭት በተቀላቀለበት መንፈስ ነገረኝ።
  እኔም ሳቅኩኝ እሱም ሳቀ በዚሁ ተለያየን።

አዎ!! ይህ አባባል የሚያስቅ ልበ ወለድ ቢመስልም የህዝቡ እሮሮ መገለጫ ነው። በዚሁ ፅሑፍ ለመጥቀስ ያስገደደኝ ምክንያት አባባሉ ከላይ የጠቀሱኩዋቸው 10 ነጥቦች በአጭሩ የአገዛዙን ገፀ ባህርይ በትክክል የሚገልፅ ሆኖ ስላገኘሁት እንጂ በነ አባ ዱላ፣ አባይ ወሉና በረከት ስምዖን ላይ የግል ጥላቻ ወይም ንቀት ስላለብኝ አይደለም። እነሱም የገዛ ክብራቸው ራሳቸው አራከሱት እንጂ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አከብራቸዋለሁ። እንደ የፓለቲካ ሰዎችና የስርዓቱ የአገዛዝ ቁንጮ አባላት በመሆናቸው ደግሞ መተቸታቸውና መጠየቃቸው የማይቀር ነው። በዚህ መሰረት እስካሁን ሲሰሩት የቆዩትና አሁንም እየፈፀሙት ያሉት አሳፋሪ ተግባር ከላይ የተጠቀሱትን 10 ነጥቦች ወራሽ ነን በማለት በራሳቸው የማይተማመኑ፣ ከጊዜ ጋር የማይራመዱ፣ ለነፃነታቸው ጥብቅና የማይቆሙ፣ የኢትዮጵያውያን የአልገዛም ባይነት ባህል ያራከሱና ኢትዮጵያዊነትን የገደሉ ናቸው። ስራቸውም ለአንድ ፈላጭ ቆራጭ መሪ በንብረትነት እንዲያገለግሉ ተብሎ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አደንዛዥ ሶፍት ዌር (**soft ware**) በጭንቅላታቸው ውስጥ የተገጠመላቸው ሰዎች ስለሆኑ አቶ መለስን ከመወደስና የሳቸውን ተግባር ከመድገም ሌላ ለዚሁ ትውልድ የሚመጥን አዲስ አማራጭ ሀሳብና ፓሊሲ ያመነጫሉ ብሎ መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ ይወለዳል ብሎ እንደ መጠበቅ ያህል ነው። “የቅል አበቃቀል እንደ ፍሬ ነው” እንደ ተባለው ሁሉ ለራሳቸው ነፃ ያልወጡ፣ ባርነት የለመዱ መሪዎች ለኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነትና የዲሞክራሲ ለውጥ ያመጣሉ ብሎ ማሰብ ዋህነት ነው። ፈረንጆች ሲተርቱ “በአርባ ዓመቱ ያበደ እስከ መቃብር ድረስ ነው” (the mad of 40 years is fool forever) ይላሉና።

ከላይ በቁጥር 1 እንደ ተጠቀሰው ከአቶ መለስ ዜናዊ ካገኘናቸው ፍልስፍናዎች አንዱ <u>ውሸት ማር ጠቅልሎ ማጉረስ</u> ነው። በሬ ወለደ ብሎ የማሳመን ችሎታና ራሱ ገርፎ ራሱ የመጮኽ ልምድ ነው። ይህንንም ገና ከደደቢት አሁዱ ብለው ትግል ሲጀምሩ የተካኑበት የማታሊያ ጥበባቸው መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ። <u>“ለዛሬ እንዋሽ ለነገ እናስብበታለን” (ንሎሚ ንሓሱ ንፅባሕ ንሓስበሉ)</u> የሚል ፓሊሲ በመከተል <u>“ውሸት ሲደጋገም ሀቂ ይመስላል”</u> የሚለው አባባል በትክክል ተግባር ላይ ያዋሉ መሪ ናቸው። ስለ አቶ መለስ የተፃፉት አንዳንድ መፃሕፍቶችም የሚያረጋግጡልን ይህንን ነው። በሀገሪኛ አባባል “ውሸተኛ ሰው እንኳን ለመሪነት ለጋብቻም አይበቃም” እየተባለ የሚነገርላት ኢትዮጵያ ዛሬ ውሸትና ሌብነት የአስተዳደር ዘይቤ ሆኖ ከማገልገል አልፎ የህዝቡ ባህልና የትምህርት ቤት መማሪያ ስርዓተ ቀለም እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ለሀቅ መቆም እንደ ሞኝነትና ወንጀለኛነት፣ መዋሸትና ሌብነት ደግሞ እንደ ብልህነት እየተቆጠረ ዛሬ “ከሳሽ ከመሆን ተከሳሽ መሆን ይቀላል” የሚባልበትን ዘመን ላይ ነው ያለነው።

የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችና ካድሬዎች ከአቶ መለስ የወረሱት ሌላው ፍልስፍና <u>የስድብና የማሸበር መርሃ ጥበብ</u> ነው። መንግስታዊና ወታደራዊ ጡንቻ መከታ በማድረግ በተለይም በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ ዜጎችን በማንቋሸሽ፣ ክብር በመደፈር፣ ሰብኣዊ መብታቸውን በመጣስና እንዲሁም የሌላውን ዜጋ ታሪክ በማራከስ የራስህን ገናናነትና ዝና መገንባት የሚል ትልቁ የጀግንነታቸውና የአሸናፊነታቸው መገለጫ መሳሪያ ሆኖ ቆይቷል። ይህንን ዜዴ በመጠቀም አቶ መለስ ከደደቢት ጀምሮ እስከ ዳግማዊ ሚኒሊክ ቤተ መንግስት ድረስ የመጡበት ጉዞ የጥሎ ማለፍ ታሪክ እንደ ነበር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ከዚሁ ልምድ በመነሳት ከአቶ መለስ የሚረዝም ሰው ወይም የበለጠ አስተሳሰብና ራእይ ያለው ዜጋ በምንም

ዓይነት በኢትዮጵያ ምድር እንዳይበቅል ጥረት ሲያደርጉ ቆይቷል። ሁሉም በሳቸው ልክ የተሰፋ ጥብቆ እንዲለብስ እየተደረገ ቆይቷል። በተለይም ወጣቱ ትውልድ የአባቶቹ ጀግንነት እንዳይወርስ፣ ሀቀኛ ታሪኩ እንዳያውቅ፣ ለሀገሩ፣ ለህዝቡና ለሰብአዊ ክብሩ ጥብቅና የሚቆምና በራሱ የሚተማመን ዜጋ እንዳይፈጠር በቀጥታም ሆነ በስውር ደባ ሲፈፀምበት ቆይቷል። ከአቶ መለስ የተለየ አመለካከት ይዞ ከተገኘ ደግሞ "ይቺ ባቁላ ካደረች አትቆረጠምም" በማለት ገና ከእንጭጩ እንዲቀጩ ይደረጋል። በነ ወ/ት ብርቱኳን ሚዴክሳ፣ አንዱለም አራጌ፣ በቀለ ገርባ፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ በዕጩ ተወዳዳሪ የነበረው አረጋዊ ገብረዮሐንስና ሌሎች ታጋዮች ላይ በኢጣሊያ የባዕድ ወረራ ጊዜ እንኳን ያልተፈፀመ ግፍ እየደረሰባቸው ይገኛል።

ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። አቶ መለስ ዜናዊ ዳግማዊ ሚኒሊክ ከገቡበት ቀን ጀምሮ እስከ ህልፈታቸው ዋዜማ ድረስ ተቀናቃኝ ሀይሎችን አንገት ለማስደፋትና ተስፋ ለማስቆረጥ ሲባል ስንት የስድብና የሽብር ቃላቶች እንደ ተፈበረኩና ስንት አሰቃቂ እርምጃዎች እንደ ተወሰዱ የሚከተሉትን ለአብነት ያህል በአጭሩ መመልከት ይቻላል።

ሀ) ከተራ ስድብ ጀምሮ እስከ አዋጆች ደረስ በዜጎች ላይ የሚለጠፉ ታርጋዎች

| | | |
|---|---|---|
| - ጭቃ | - ነፍጠኞች | - ፀረ ሰላም ሀይሎች |
| - ገለባዎች | - ወንጀለኞች | - ፀረ ልማት ሀይሎች |
| - የበከቱ | - አክራሪ ሀይሎች | - የደርግ ስርዓት ናፋቂዎች |
| - የሻዕቢያ ተላላኪዎች | - ነውጠኞች | - ሕገ መንግስቱን የሚንዱ |
| - ሽብርተኞች | - ጦርነት ናፋቂዎች | - የውጭ ሀይል ቅጥረኞች |
| - ትምክሕተኞች | - የጥፋት ሀይሎች | የሚሉ ናቸው። |

- ሞት ይፈረድባቸዋል፣ ዕድሜ ይፍታሕ ይታሰራሉ፣ ጣታቸው ይቆረጣሉ፣ ሀብታቸው ይወረሳል
- ከሽብርተኞች ጋር አብሮ ቡና ሻይ የጠጣ አብሮ ይደቆሳል የሚሉ እንደ ጦር የሚወረወሩ ቃላቶች ሰምተናል።

ለ) ምርጫ በተቃረበ ቁጥር ደግሞ ለህዝቡ የሚነገር የሽብርና አስደንጋጭ ፕሮፓጋንዳ፡-

- እኛ ካልተመረጥንና ስልጣን ላይ ከሌለን እንደ ሩዋንዳ ኢንተርሃሞይና አርማጌዶን ይፈጠራል
- እኛ በስልጣን ላይ ከሌለን ሀገሪትዋ ትበታተናለች፣ ጦርነት ይነሳል፣ የደርግ ስርዓት ተመልሶ ይመጣል
- እኛ ካልተመረጥንና ስልጣን ላይ ከሌለን የኦነግ፣ የሻዕቢያና የሽብርተኞች ዒላማ ትሆናለህ
- ህወሓት/ኢሕአዴግ ካልመረጥክ ቤትህ ይወረሳል፣ መሬትህ ትነጠቃለህ፣ የውጭ እርዳታ አታገኝም፣ ከስራህ ትባረራለህ፣ የንግድ ፍቃድህ ይነጠቃል የሚል ቤት ለቤት እየተንኳኳ ይሰራጫል።

ሐ) ለህወሓት/ኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎቻቸው የሚነገር የሽብርና የማስደንግጥ ፕሮፓጋንዳ፡-

- እኛ ካልተመረጥንና ስልጣን ላይ ከሌለን በትግላችሁ ያገኛችሁትን ጥቅም ትነጠቃላችሁ
- እኛ ካልተመረጥን ያገኛችሁትን ስልጣን ወይም ጥቅም በነፃ ገበያ ተወዳድራችሁ አታገኙትም
- እኛ ካልተመረጥና ስልጣን ላይ ከሌለን የታገልንበትን አላማ በጥፋት ሀይሎች ይነጠቃል
- ሕገ መንግስታችን ይናዳል፣ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተነጥቆ የአማራ የበላይነት ዳግም ይነግሳል
- የሰማእታት አደራና ሐወልት ይፈርሳል፣ ወዘተ በማለት በየደረጃው ይነገረዋል።

መ) በሀይማኖት፣ በብሄር ብሄረሰቦችና በማሕበራዊ ነክ ጉዳዮች ያነጣጠረ የማሸበር ፕሮፓጋንዳ፡-

- ሀይማኖት ከመንግስት ነፃ እንደሆነ ሕገ መንግስቱ ይጠቅሳል። መሪዎቹም በቃል ደረጃ ይናገራሉ። ነገር ግን በተግባር ሲታይ ሀይማኖት የፓለቲካና የለያይተህ ግዛ መሳሪያ አድርገው ሲጠቀሙበት ይታያሉ። በአንድ በኩል በተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ጣልቃ እየገቡ ጳጳስ ከጳጳስ ጋር እያጋጩ የምእመናኑ አስተዳደር ራሱ የውጭና የሀገር ውስጥ ሲኖዶስ ተብሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሁለት ጎራ የተከፈለው በአቶ መለስ አገዛዝ ዘመን ነው። ከዚያም አልፈው ካድሬዎች አሰርገው እያስገቡ የሀይማኖነቱ ስነ ስርዓት ዓውደ ብጥብጥና ንትርክ እንዲሆን ሌት ተቀን ይጥራሉ።

- በሌላ በኩል ደግሞ ለብዙ ዘመናት ተፋቅረውና ተቻችለው በአንዲት እናት ሀገር በወንድማማችነት የኖሩ የክርስትና አማኞችንና ሙስሊም ወገኖቻችንን ለማጋጨት ያልፈነቀሉት ድንጋይና ያልጫሩት እሳት የለም። ከዚያም አልፈው በሙስሊሙ ሕብረተሰብ መካከል ጣልቃ በመግባት የእምነት ነፃነታችን ይከበር ስላሉ ብቻ ግማሹ በአክራሪነትና በሽብርተኝነት በመፈረጅ ሌላው ደግሞ የመንግስት ድጋፍና የሕግ ከለላ በመስጠት

እርስ በራሳቸው ለማባላት ሲጥሩ መቆየታቸው የአደባባይ ሚስጢር ነው። በሌላ አነጋገር ግማሹ ሙስሊም የስርዓቱ ታማኝ ሌላው ደግሞ ሙብቱ የተነጠቀ ሁለተኛ ዜጋ አድርገው በመፈረጅ፣ በመግደል፣ በማሰርና በማስፈራራት ስራ ላይ ተጠምደው መቆየታቸው ይታወሳል። ሰሞኑን መንግስት የሀይማኖት ጣልቃ ገብነቱን በመቀጠል በደቡብ ወሎ የገርባ ከተማ ነዋሪዎች የሆኑት ሙስሊም ወንድሞቻችን ላይ በመስጊዳቸው እንዳሉ ጥቃት በመሰንዘር የተገደሉና የቆሰሉ እንዳሉ ታውቋል። ይህ አረሜናዊ ድርጊትም ከአቶ መለስ ዜናዊ ስርዓት የባሰ ጨካኝ ጉግ ማንጉግ እየተፈጠረ እንደሆነ አማላካች ነው። አሁንም በቀጣይነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ወንድሞቻችን በገዛ ሀገራቸው የመምረጥና የመመረጥ ሙብታቸው ተነፍገው በስጋት ላይ የወደቁ ምእመናን በየመሲጊዱ ከመጮኽ አልፎ በመንግስት ታጣቂዎች ግድያና ድብደባ እየደረሰባቸው እንደሆነ ዓለምም ጭምር እየመሰከረላቸው ይገኛል። በሀገራችን ይህ ዓይነቱ ስጋት፣ ሽብር፣ ብጥብጥና ትርምስም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው በአቶ መለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን ነው።

- ሌላው የለያይተህና አናቁረህ ግዛ ፍልስፍናቸው ብሄር ከብሄር ጋር ማጋጨትና ማቃቃር ነው። ይህ ስልትም ለሁለት ነገር ይጠቀሙበታል። አንዱ የህዝቡን ልብ ማስሸፈትና ኢትዮጵያዊነትን ማዳከም ነው። ሁለተኛው ደግሞ ህዝቡ ተባብሮ አንድነቱን፣ ሉዓላዊነቱን፣ ሰብአዊ ክብሩን፣ ማንነቱንና ነፃነቱን እንዳያስከብር ዓቅሙን አዳክሞና በታትኖ ጨቆኖ ለመግዛት የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው። በተለይም የፓለቲካ ቁማር ጨዋታቸው ማእከል ያደረጉት በትግራይ፣ በአማራና በኦሮሞ ህዝብ መካከል ክፍተት ለመፍጠር ነው። የትግራይ ህዝብ የፈጠሩት እነሱ፣ ታሪኩም ከደደቢት የሚጀምር አድርገው በመቁጠር መፃኢ ዕድሉም የህወሓት መሪዎች በስልጣን ሲኖሩ የሚኖር ድርጅቱ ከጠፋ ደግሞ አብሮ የሚጠፋ ህዝብ ተደርጎ ይነገረዋል። በሌላ አነጋገር የህወሓት መሪዎች ስልጣን ላይ ከሌሉ የአማራ ትምክህት፣ ኦነግና ሻዕቢያ ይበላሃል ማለታቸው ነው። ሁለት ስለት ያለው ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ለኦሮሞ ህዝብ ደግሞ ኢሕአዴግ ከሌለ የአማራ ነፍጠኛ ተመልሶ ስልጣን ላይ ይመጣል፣ መሬትህ ተነጥቆ ወደ ጢሰኝነት ትመለሳለህ በማለት በአማራ ህዝብ ላይ ስጋት እንዲኖረው ማድረግ ስራዬ ብለው ተያይዘውታል። ወደ አማራው ሲሄዱ ደግሞ ኦነግ ስልጣን ላይ ከወጣ የአማራ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አናሳ ብሄር ብሄረሰቦችንም ጭምር ቂም ይበቀላል እያሉ የአማራ ህዝብ በኦሮሞ ወንዱሙ ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው ይጥራሉ።

- በዜጎች መካከል ቅራኔ፣ ጥርጣሬ፣ ሽብርና ፍርሃት እንዲነግስ ማድረግ በብሄርና በሀይማኖት ብቻ የተወሰነ አይደለም። መንግስት አውራጃ ለአውራጃ ከዚያም ወርዶ በቤተሰብ የግል ማሕበራዊ ጉዳይም ጣልቃ ይገባል። በተለይም በትግራይ አካባቢ ተቃዋሚ ናችሁ በማለት የቤተሰብ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሂይወት በማፍረስ በሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የተፈናቀሉበት ድርጊት ነው። ለምሳሌ የቤተሰብ ሽንጎ ከማቋቋም ጀምሮ እስከ ባልና ሚስት ማፋታት ትልቁ የህወሓት ካድሬ የዕለት ተሌት ስራ ነው። ባል የህወሓት አባል ሆኖ ሚስቱ ደጋፊ ካልሆነች ወይም ሚስት ደጋፊ ሆና ባልዋ ተቃዋሚ ከሆነ መጀመሪያ በምክር፣ ሁለተኛ በግምገማ፣ በግምገማ ካልተሳካ ደግሞ መጨረሻ በተለያየ መልኩ ትዳሩ እንዲፈርስ ይደረጋል። ሁሉም ቤተሰብ ደጋፊ ካልሆነ ደግሞ የተቃዋሚ ዘር (ተቓዋሚ ዓሌት) ተብሎ መንግስት ከሚሰጠው ጥቅማ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ከሕብረተሰቡም እንዲገለልና በጠላትነት እንዲታይ ይደረጋል። በዚሁ አሸባሪ ድርጊት ምክንያት ለህይወታቸው የሰጉ በሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ሀገር ለቀው ተሰደዷል፣ ታስረዋል፣ ደብዛቸው ጠፍቷል።

ሰ) በአቶ መለስ ዜናዊ የአገዛዝ ፍልስፍና ስሌት መሰረት 90 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ወዳጅና ጠላት ተብሎ የተከፈለ ነው። ወዳጅ የሚባለው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ርእዮተ ዓለም ተጠምቆ የህወሓት/ኢሕአዴግ ልማታዊ መንግስት አባልና ደጋፊ ናቸው። ማህል ሰፋሪ ብለው የሚጠሩት ሰፊው ህዝብ ሲሆን በጠላትነት የተፈረጀው ደግሞ በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፈ ዜጋ ነው። የተለየ አማራጭ ሀሳብና ፓሊሲ ይዞ መደራጀትና መንቀሳቀስ በሕገ መንግስቱ የሰፈረ ሙብት ቢሆንም ይህንን ሙብት ለማሳጣትና ህዝቡን ለማደናገር ሲሉ መቃወም ማለት የጠላትነት ሽፋኝ በመስጠት ከላይ የተጠቀሱትን የስድብና የስም ማጥፋት ታርጋ በመለጠፍ ተቃዋሚውን ሁሉ በጀሞላ ያሳድዳሉ። ሆኖም "ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኻል" እንዲሉ

- ሕገ መንግስትን የሚጌዱትና የሚጥሱት የስርዓቱ መሪዎች ሆኖ ሳለ፣ በተገላቢጦሽ ተቃዋሚዎችን ያወግዛሉ።
- የሀገሪቱን አንጡራ ሃብት የሚዘርፉ የስርዓቱ መሪዎችና ካድሬዎች ሆኖ ሳለ፣ በአንፃሩ ሙሱና ይጥፋ፣ ሌቦችም ለፍርድ ይቅረቡ ብለው የሚጮኹ ተቃዋሚዎች ያስራሉ ይገድላሉ።
- ህዝቡን ነጋ ጠባ በተለያዩ አዋጆች የሚያሸብሩ እነሱ ራሳቸው ሆኖ ሳለ፣ ተቃዋሚውን ሽብርተኛ ብለው ይከሳሉ።

- ከሻዕቢያ ጋር አብረው ሀገርንና ወገንን ሲያደሙ የነበሩት የህወሓት መሪዎች እነርሱ ራሳቸው ሆኖ ሳለ ሳይቀድሙን እንቅደማቸው በሚል በተገላቢጦሽ ሌላውን ወገን የሻዕቢያ ተላላኪ ይላሉ።
- በአደባባይ የዜጎችን ሰብአዊ ክብርና መብት በመጣስ የሚሳደቡ፣ የሚያንቋሽሹና የሚዘልፉ እነሱ ሆኖ ሳለ፣ በአንፃሩ ተቃዋሚዎችን አፍ እላፊ እያሉ ወደ እስር ቤት ይወረውራሉ።
- ከሻዕቢያ፣ ከኦነግና ከኡጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) ጋር ያለ ቅድመ ሁኔታ መደራደር እንችላለን ብለው የሚናገሩና የሚጥሩ እነሱ ሆኖ ሳለ፣ ነገር ግን በሀገር ውስጥ በሰላምና በሕጋዊ መንገድ ከሚታገሉ ከነ "መድረክ" ጋር በጋራ ሀገራዊ ጉዳይ ለመደራደር ይፀየፋሉ።

ከላይ የተጠቀሱትን ስድቦችና ማስፈራሪያዎች በቃላት ብቻ ተነግረው የሚያበቁ አይደሉም። ለዚህ ማስፈፀሚያ ተብሎ በአቶ መለስ ፓሊሲና ራእይ መሰረት አድርጎ ህዝቡ አንድ ለአምስት ተዋቅረዋል። በመቶ የሚቆጠሩ የዜጎች መብት ገዳቢ አዋጆችና መመሪያዎች ተደንግገዋል። ከተማሪ ቁጥር በላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ካድሬዎች በየቦታው ተመልምለዋል። በየወረዳው በሽህ የሚቆጠሩ በመንግስት ሰራተኛ ሽፋን ደመወዝ እየተከፈላቸው በጋሃድም ሆነ በስውር ለስለላና ለአፈና ስራ የሚያገለግሉ ተሰማርቷል። በብዙ ቢሊዮን የሚገመት የሀገሪቱ አንጡራ ሃብት በተለያየ መልኩ ለአፈናና ለስለላ ይውላል። የግል ሚዲያ ታማኝ ከሚባሉት በስተቀር ብዙዎቹ ተዘግቷል። መንግስታዊ ያልሆኑ የህዝብ ማሕበራትና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አብዛኞቹ ተዘግቷል። የቀሩትም የሰንበቴ ማሕበር ሳይቀር በመንግስት እይታ ስር እንዲገቡ ተደርጓል። በሕገ መንግስቱ የሰፈረው ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት ተዘግቷል። ዛሬ ሰላማዊ ሰልፍ ማድርግ ቀርቶ የስብሰባ አደራሽ ለመከራየትም የተገደበ ሆኗል። በሕግ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሕግ ከለላ የላቸውም። አባላቶቻቸው ያለም ምንም ጥያቄ ይደበደባሉ፣ ይታሰራሉ። ፅሕፈት ቤታቸው በየጊዜው ይዘጋል፣ ይዘረፋል፣ ይፈርሳል፣ ይሰለላል።

ቁልፍ የሆኑ የመንግስት መዋቅሮች ከላይ እስከ ታች በታማኝ የህወሓት/ኢሕአዴግ አባላትና ካድሬዎች ተይዘዋል። በሀገሪትዋ ውስጥ ያሉት ርእሰ መምህራንና ምክትል በሙሉ የገዢው ፓርቲ አባላት ናቸው። ሌሎች ተራ መምህራንና ተማሪዎችም የስርዓቱ አባላት እንዲሆኑ አየተገደዱ ናቸው። የመማሪያ ስርዓተ ትምህርቱም ከላይ የተጠቀሱት 10 ነጥቦች መሰረት አድርጎ የወጣ ነው። የብዙሃን መገናኛ ነጋ ጠባ ከባለስልጣናቱ የሚነገረው የውሸት ፕሮፓጋንዳ ከመስማት ውጭ ህዝቡ ሌላ አማራጭ የለውም። እንደ የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮና የጀርመን ድምፅ ራዲዮ የመሳሰሉት ገለልተኛ የብዙሃን መገናኛ ሚዲያዎችም ሳይቀር በኢትዮጵያ እንዳይሰራጩና ህዝቡ አማራጭ ዜና እንዳይሰማ በየቀኑ በሚሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ ለውጭ ስርጭት ማፈኛ በጀት ይውላል። የፍትሕ፣ የዳኝነትና የምርጫ ቦርድ የሚባሉ ተቋማት የገዢው ፓርቲ ቅርጫፍ ፅሕፈት ቤት ከመሆን የዘለሉ አይደሉም። ሕገ መንግስቱ፣ ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ ፈፃሚ አካላት በሙሉ የገዢው ፓርቲ አጃቢና ትእዛዝ ተቀባይ ከመሆን አልፈው የህዝቡ እሮሮና ጥያቄ ሰሚና የሀገሪቱ ብሄራዊ ጥቅም ጠባቂ አይደሉም።

የዚህ ሁሉም ስንክሳራዊና አስገራሚ ተግባር ኢንጅነር የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ናቸው። ስልጣናቸውን ዘላለማዊ ለማድረግ በተለያየ ስልትና ስትራተጂ፣ በተለያየ ስድብና ማስፈራሪያ፣ በመግደል፣ በማሰርና በማባረር የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ለማዳፈን፣ ተስፋ ለማጨለም፣ ለማንበርከክና ለማታለል ሲባል እንቅልፍ አጥተው ጥረት ቢያደርጉም ነገር ግን እግዚአብሄርን ማታለልና ማደናገር አይቻልምና መቶ ዓመት ሳይነግሱ ባልጠበቁት ጊዜ በ57 ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም አልፏል።

እንግዲህ!! አሁን ጥያቄው ከዚህ በኋላ የሀገራችን መፃኢ ዕድል ምንድን ነው? ነው። የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ያለፈውን ይቅር በማለት የሽብር አዋጆች በሰላም ጥሪ አዋጅ ቀይረው ከህዝቡ ጋር ተቻችለውና ተከባብረው ይችን ድሃ ሀገር ማስተዳደርና በሰላም መኖር እየቻሉ ለምን ከላይ የተጠቀሱትን ውስብስብ ችግሮች መግባት ይመርጣሉ? የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ለህዝብና ለሀገር የሚጠቅም አላማ፣ ፓሊሲና ሞራል ካላቸው በጡንቻና በዘመቻ ከመግዛት ይልቅ ህዝብና ትውልድ ሊማርበት በሚችል መልኩ በነፃ መድረክ ቀርበው በግልፅ በመከራከር በህዝቡ ዘንድ ለመዳኘትና የሕግ ልዕልና ለመቀበል ለምን ያስፈራቸዋል? በአንድ ሀገር የሰለጠነ መንግስትና የሰለጠነ ተቃዋሚ መኖር ከሁሉም በላይ ተጠቃሚው ማን ነው? አልጋ ወራሽ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ማሓላ የፈፀሙት የአቶ መለስ ቃል ለማክበር ወይስ የህዝብ አደራ ለመጠበቅ? ለመሆኑ ታላቅና ጀግና የምንላቸው ያሀገርና የፓለቲካ መሪዎች መለኪያችን ምንድን ነው? አሁን በመደነጋገር ላይ ያለው መንግስት ከአቶ መለስ አገዛዝ ይሻላል ወይስ ይብሳል? የሚሉና ሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በመዳሰስ በሚቀጥለው ክፍል ሁለት ፅሑፌ እስከምንገናኝ ድረስ ደህና ሰንብቱ።

ሃያሉ እግዚአብሄር ሀገራችንን ይጠብቅ